<u>የካቲት 10 ቀን 2001 ዓ.ም</u>

የር/ዓ/ለ/ደ/ጽ/ቅ/ማ/ቤ/ክ ሰ/መ/አ/ጉባዔ
<u>ለንደን።</u>

<u>ጉዳዩ፡</u> *ጥር 30 ቀን በሰ/ጉባዔው ተጻፈ የሚል፡ ስም የሌለው ፊርማ ያዘለውን ሕገ-ወጥ የሃሰት ስም ማጥፊያ ደብዳቤን ይመለከታል፤*

በቅድሚያ አምላካችን ማስተዋልንና እምነትን እንዲሰጣችሁ በመጸለይ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ።

በመሰረቱ ስም የሌለው ፊርማ ላዘለ ሕገ-ወጥ ደብዳቤ መልስ መስጠት አስፈላጊ ባይሆንም፣ በሰ/ጉባዔው ስም በመጻፉ፣ ከኋላው ያዘለውን የሃሰት አሉባልታ አላማ ለማሳየት፣ በሕገወጥነት በጽ/ቤቱ በተቀመጡ ግለሰቦች የቤ/ክችን ማህተም ለምን አይነት ሰይጣናዊ ስራ እየዋለ መሆኑን ለማጋለጥ፤ የቤ/ክኑ ሕግና ሥነሥዓርት ጉባዔ እርምጃ እንዲውስድና የቤ/ክኑ ካህናትና ምእመናን እንዲያውቁት ጭምር ለማድረግ መልስ ለመስጠት ተገድጃለሁ።

<u>ሀ. የካህናት ጉባዔ ቃለ-ጉባዔና ውሳኔን በተመለከተ፤</u>
ሐምሌ 27 2000 ዓ.ም የሰ/ኣ/ጉባዔው እንዲያውቀው በግልባጭ የተሰጠውን፤ የካህናት ጉባዔ አባላት ተወያይተው በፊርማቸው ያጸደቁትን ቃለ ጉባዔ ... *መስከረም 25 2001 ዓ.ም በጻፍነው ደብዳቤ ዕንዳልተቀበልነው ገልጸናል፤...* ይላል።

የደብዳቤው ጸሐፊ በቤ/ክችን ውስጠ ደንብ መሰረት፣ ሥርዓተ ቤ/ክና ምስጢራተ ቤ/ክንን የሚመለከት ውሳኔ በሙሉ የካህናት ጉባዔው መሆኑን ካለመረዳቱም በላይ፣ በግልባጭ እንዲያውቀው ለተሰጠ ደብዳቤ ባለቤቱ እኔ ነኝ ለማለትም የሞከረ ይመስላል። የሆነሆኖ፤ መስከረም 25 2001 ዓ.ም በመ/ጽ/ቀ/አባ ግርማ የተጻፈው ደብዳቤ ስለ ሰበካ ጉባዔ ውይይትም ሆነ ውሳኔ የገለጸው ነገር አለመኖሩና፤ ግለሰቡ በካህናት ጉባዔ ሰብሳቢነታቸው የጻፉት መሆኑን በመረዳት፣ ስላፈጻጸሙም ሆነ ማእከላዊ አሰራርን በተመለከተ ከበቂ መረጃ ጋር፣ እንደቀረበው የሃሰት ክስ የቃላት ድርድር ሳይሆን፣ የቤ/ክችንን ውስጠ ደንብ በመጥቀስ ባጭሩ መልስ ሰጥቼበታለሁ። በዚህም መሰረት፤ ላቀረቡት ክስ መረጃቸውን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ጉዳዩ ለሚመለከተው የካህናት ጉባዔ ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው፣ ክሱ የሃሰት ስም ማጥፍያ መሆኑ ተረጋጧል። በተጨማሪም፣ ይህ መልኩን ቀይሮ የመጣ ሕገወጥ የማጭበርበሪያ ጽሁፍም፣ አቅጣጫን በመቀያየር የተያዘውን ስም የማጥፋት ዘመቻ  አላማ በግልጽ አሳይቷል። የካህናት ቃለጉባዔን በተመለከተ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የካህናት ጉባዔም የሥነሥርዓት ውሳኔ እርምጃ እንዲወስድም ጠይቄ በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ።

ከዚህ ውጭ በግልም ይሁን በቡድን፣ የቤ/ክ አገልጋዮች ካህናትና የሰ/ት/ቤት መዘምራን ከሌሎች የኢ/ኦ/ተ/አብያተ ክርስቲያናትና አባቶች ጋር ማገልገል አትችሉም የሚል ቢኖር፣ ሃሳቡን በሌላ ሳያስታክክ በቀጥታ ለቤ/ክችን የካህናት ጉባዔ ማቅርብ እንደሚችል በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

**ለ. በደብዳቤው የቀረቡትን አዲስ የሃሰት ስም ማጥፊያ ሙከራዎችን በተመለከተ፤**

በርእስነት ከተያዘው ጉዳይ ውጭ፣ በተለጣፊነት ሁለት አዳዲስ የሃሰት ስም ማጥፊያ ውንጅላዎች ተጽፈው ተበትነዋል። በእርግጥ ከዚህ በፊት የተሞከሩ የሃሰት ውንጅላዎች በሙሉ ፍሬቢስ ሆነው በመቅረታቸውና፣ ፤ሌላ እኔን የመወንጀያ ሰበብ ቆፍረው ውለው ቢያድሩ ባለመገኘቱ፣ የጻፈው ክፍል/ግለሰብ *የደብሩ ሰ/መ/አ/ጉ ጸሐፊ ሆነህ ስትሰራ በሰብሰባ ላይ እንዲህ ተብሏል፣ እንዲህ ሰንወያይ ነበር?...* በማለት፤ በተቀደሰው ቦታ ሆነው፣ የሃሰት አሉባልታና ስም ማጥፍያ ሲደርድሩና፣ የመለያትና የመከፋፍል እኩይ ተግባራትን ሲፈጽሙ፤ አንዳችም ሃፍረት አልተስማቸውም። እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው!

1. *በአስተዳዳሪውና በሌሎችም ስም የተልያየ ሕገውጥ ደብዳቤ ጽፈሃል* .......
የለሚለው በተመለከተ፤

ክሱ በእርግጥ አስቂኝ ፈጠራ ነው! በጊዜው ይህን ሁሉ ህገ-ወጥ መጻጻፍ ሳደርግ በሰ/አ/ጉባዔውም ሆን በህግና ለሥነ ሥርዓት ኮሚቴ በወቅቱ እርምጃ እንዲውሰድብኝ ያልተደረገው ለምን ይሆን? የቤ/ክኑ ፋይል በጽ/ቤቱ ኮምፒውተርና ኮፒው በእኔ ዘንድ ይገኛል፤ ምነው ተጠርቼስ አለመጠየቄ? እኔ አሁን ያለውን የደብሩን ጽ/ቤት በዘመናዊ መልክ ከማደራጀት ጅምሮ እስከ ቤ/ክኑ ግዢ ድረስ በገባሁት ቃል መሰረት ሃላፊነቴን ተወጥቼ፤ በግዛ ፈቃዴ የጸሐፊነቱን ቦታ ከለቀቅሁ ሁለት ዓመት ሊሞላ ነው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ይህ ሁሉ ህግወጥ ስራ ሲፈጸም ከሳሶቹ የት ነበሩ? አስገራሚ ነው? እኔ በስራ ዘመኔ ሕገ-ወጠችን ከማረም በስተቀር የጻፍኩትም ሆነ የፈጸምኩት ምንም ዓይነት ህገ ውጥ ተግባር እንደሌለ አብረውኝ የሰሩ ሁሉ የሚያውቁት ሃቅ ነው።

ይህ አይን ያወጣ የሃሰት ስም ማጥፊያ ዘመቻ በቤ/ክን ቦታ የሌለውና ከእውነተኛ ካህናትና ምእመናን የማይጠበቅ ተግባር መሆኑን ደግሜ ለማስገንዘብ እወዳለሁ። እንዲህ ያለ ወንጀል ስለመፈጸሜ መረጃ ካለ፤ በቤ/ክናችንም ሆን በሃገሪቱ ህግ መሰረት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንድጠየቅ ማድረግ ተገቢ ነውና፣ ክሱን ከነመረጃው ለሚመለከተው ክፍል እንዲቀርብ ስል አሳስባለሁ። ከዚህም ጋር፣ ቀደም ሲል በቤ/ክኑ ጽ/ቤት ባሉ ግለሰቦች ከካህናት መዝገብ ፊርማዬ በፎርጀሪ ተወስዶ ከሌላ ጽሁፍ ጋር በማገናኘት በኢንተርኔትና በኢሜይል ስሜን ለማጥፋት የተበተነውን መረጃ አብሮ እንዲታይልኝ ይዤ እቀርባለሁ። ከዚህ ውጭ ግን ራስ ከሳሽና ዳኛ በመሆን የሰውን መብት መድፈርና፤ ረብ የሌለው ተራ አሉባልታ በቤ/ክኑ ማህተም እያተሙ መበተን ከፍተኛ ወንጀል መሆንኑና፣ እያንዳንዱ ፈራሚና አታሚ በግል እንደሚጠየቅበት ለማሳሰብ እወዳለሁ። የቤ/ክ አርማና ማህተምም ለመንፈሳዊና ለተቀደሰ ተግባር እንጂ፡ ለንዲህ ዓይነቱ አጸያፊ ተግባር መዋል እንደሌለበት በጥብቅ አሳስባለሁ።

2. *በቤ/ክን ግዢ ሂደት ወቅት ግንኙነቱ በኔ በጸሃፊው በኩል እንዲሆን ብለህ ጽፈሃል* ...
ለተባለው፤

በወቅቱ የቤ/ክኑ ግዢ ሂደት መጻጻፍ ከጽ/ቤቱ ውጭ በግልሰብ መኖሪያ ቤት መካሄዱ ሕጋዊና ተገቢ አለመሆኑን የጽቤቱን ስራ ከጅመሩኩ ቀን አንስቶ ባሳስብም፤ የተለያሁ ምክንያቶች እየቀረቡ ወደ ግዢው መገባድጃ መደረሱ ይታውሳል። በዚያ ወሳኝ ወቅት ተላከልን/በስልክ ተነገረን ወዘተ... እየተባሉ ለሰ/መ/አ/ጉባዔው የሚቀርቡ መረጃዎች በተደጋጋሚ ከእውነታው ጋር በመጋጨታቸው በውስጥ መ/ደንባችን አንቀጽ 17 (7) እና (8) መሰረት የመረጃ ግንኙነቱ

በቀጥታ ከደብሩ ጽ/ቤት ጋር እንዲሆን መጠየቄና የሻጩ ክፍል ጋር ተነጋግሬ ማሳወቄ፣ የቤ/ክናችን ግዢ መስመሩን ስቶ ሊገባ ከነበረበት ወጥመድ ሊያመልጥ መቻሉ አይዘነጋም። ይህም ሕጋዊና ኀላፊነትን በብቃት መወጣት ነው።

እጅግ በጣም አስድንጋጭ የነበረው ክስተት ግን፤ ከሻጩች ጋር ልንፈራረም ቀናት ሲቀሩን፤ በዕለተ ሰንበት በጽ/ቤት ባለጉዳይ እያነጋገርኩ ሳለሁ፡ የግዢው ፊርማ፣ የደብሩ አስተዳዳሪም ሆነ ጽ/ቤቱ ሳያውቀው፣ 3 የሰ/ጉባዔ አባላት ትረስቲዎች ነን በማለት የፈረሙበት ስለሆነ፤ 1.2 ሚሊዮን ገደማ የሚደርስ የቤ/ክኑ ብር ወጪ እንዲሆን ከጽ/ቤቱ ውጭ ተዘጋጅቶ የመጣውን ደብዳቤ በማህተም እንዳጸድቅ በተጠየቅሁ ጊዜ ነበር። ይህን ሕገ-ወጥ ተግባር አስቁሜ ከብዙ ውጣውረድ በኋላ በአምላካችን እርዳታ፡ ቤ/ክናችንን በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ስምና፣ ጠቅላላ ጉባዔውን በመወከል በሁላችንም የሰ/መ/አ/ጉባዔ አባላት ፊርማ ለመግዛት ችለናል።

የዛሬን አያድርገውና፤ በጊዜው ከደብሩ አስተዳዳሪ ጀምሮ በጉዳዩ ዙሪያ የተሳተፉ ሁሉ፣ ቤ/ክችንን ከጉድ አወጣሃት! በማለት ያቀረቡልኝ ምስጋና አይረሳም። ይህ በታቦተ ጽዮን የተፈጸመ ገድል በመሆኑ፣ ካለፈው ለመማር ይረዳል፣ አስፈላጊ ነው ከተባለ መረጃዎችን አገላብጦ በየግልሰብ የተፈጸመውን ተግባር አንድባንድ ተንትኖ ለካህናትና ለምእመናን እንዳስፈላጊነቱ ማቅረብ ይቻላል። የወንድምን ገበና ላለመግልጥ መረጃዎች በእጄ እያሉ በትዕግስት ሳለሁ፤ አሁን በጽሁፍ ለተነዛብኝ የሃሰት አሉባላታ መልስ መስጠት ስላለብኝ ብቻ ከላይ ያለውን እውነታ ለመግለጽ ተገድጃለሁ።

ከዚህ በተረፈ፤ እኔ በደብሩ ዋና ጸሐፊ ሆኘ ባገለገልኩበት ውቅት፤ ከነበረኝ መደበኛ ስራ በተጨማሪ ቤ/ክችንን በበለጠ ለማሳደግ በግሌ ብዙ ስራዎችን የሰራሁ ሲሆን፣ ለማስታወስ ያህል፤

- የደብሩን ጽ/ቤት በቪክሬጅ መመስረትና በማደራጀት፤
- ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፋክስ ማሽኖችንና የተለያዩ የኔትውርክ እቃዎችን ምንም ወጪ ከቤ/ክናችን ሳይወጣ፤ ከራሴና ከወዳጆቼ በማሰባሰብ ዘመናዊ የኮምፒውተር ኔትወርክ በጽ/ቤቱ በመዘርጋት፤
- ከ40000 በላይ ተጠቃሚ በአንዴ ማስተናገድ ይሚችል ፍይል፣ ፕሪንትና ኢሜይል ሰርቨር ከመስሪያ ቤት በነጻ በማምጣትና ኮንፊገር አድርጌ ለጽ/ቤቱና ለቤ/ክኑ ስራ እንዲውል በማድረግ፤
- የተለያሁ የግል ሶፍትዌሮቼንና ኮንፊግ ቱልስ በመጫንና ማቀናጀት፤
- ቀደም ሲል በ1989 አካባቢ ከዲ.ደረጃ ጋር የሰራነውን የደብሩን የአባላት ዳታ ቤዝ አድሶ በኔትወርክ በማሰራት፤
- ለሰ/ት/ቤትና ለንዑሳን ኮሚቴዎች አግልግሎት የሚውሉ ኮምፒውተሮችን ዋና ዋና ሶፍትዌሮችን በማስመጣትና በመጫን ለቤ/ክ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ፤
- የጥምቅትና የጋብቻ ስርተፊኬቶችን በዴታ ቤዝ ዲዛይን ሰርቼ፣ በኮምፒውተር እንዲታተሙና ሪከርዱም በኔትወር ፊይል እንዲያዝ በማድረግ፤
- ምእመናን ስርዓተ ቅዳሴውን በስክሪን እንዲከታተሉና እንዲካፈሉ ከአሜሪካን ሀገር ከወዳጆቼ ሙሉ ቅዳሴ ፒፒቲውን አስመጥቼ በሰራ ላይ እንዲውል በማድረግ፤
- የግል መገልገዬ የነበረውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሳይቀር ለስክሪንና ፕሮጀክተር ፊድ፣ ስርዓተ ቅዳሴና ሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች እስካሁን ድረስ በቋሚነት እንዲተላለፉበት ለቤ/ክን በማበርከት፤

- ለቤ/ክናች ቋሚ ቤተልሔምና የንዋየ ቅዱሳት ማስቀመጫ ከቤተ መቅደሱ በስተቀኝ ከነበረው ክፍል በመመስረት መንፈሳዊ አግልግሎቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈም ማድረግና፤
- በተጨማሪም፤ ከቅኔ ማህሌት አንስቶ እስከ ቤተ መቅደስ ድርስ በዚህ ጽሁፍ ልገልጽ የማልችላቸውን አያሌ የምስጢራት ቤ/ክና ሌሎች ስራዎችን በእግዚያብሔር እርዳታ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማከናወን፤ ቤ/ክኔን እግዚአብሔር በሰጠኝ እውቀትና ሃብት ማገልገሌ ሁሉም የሚያውቀው፤ የታየና የተዳሰሰ ሃቅ ነው።

በዚህ የስራ ወቅት፡ በየጊዜው በቤ/ክን ውስጥ የሚነሱ ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ በማድረግ፣ በውጭ በቤ/ክችን ላይ ተንስቶ የነበረውን ፈተና በመቋቋም፣ ሕንጻ ቤ/ክኑ እንዲገዛና፣ በካህናትና ምእመናን መካከል ምንም ልዩነት ሳይኖር፣ በፍቅር በአንድነት ቤ/ክናችን በመምራት መሠረት በማስያዝ የተጣለብኝን አደራ በብቃት ተወጥቻለሁ።

ዛሬ ግን በጽ/ቤቱ በሕገውጥነትና በጉልበት ተቀምጠው ያሉ፤ እንኳን እንዲህ ሊሰሩ፡
የቤ/ክናችንን ውስጠ ደንብ በማፋልስ ሕግን በማናሉብኝነት የሚጥሱ፤
ካህናትንና ምእመናንን ከመከፋፈል እኩይ ተግባራቸው በምክር የማይመልሱ፤
ተቀጣሪ እኛ፣ ሰባኪውም እኛ፣ ባያውቁትም እንኳን ቅዳሴውም የኛ፣ አንፍልግም ሌላ ብለው የተነሱ፤ በመድረክ ወንጌል እንሰብካለን እያሉ፣ የሃስት ውንጅላ በሚገርም ሁኔታ በቃልም በጽሁፍ የሚያናፍሱ፤ በወንድማማች ፍቅር ከመወያየትና አብሮ መስራት ይልቅ፣ ለክስና ስም ማጥፋት፣ ስደ ማሳደድ የተንሱ፤ ሆነውባት ቤ/ክን ትልቅ ችግር ላይ ትገኛለች።

*ቤ/ክኗን ቦርድ ሊያደርጓት ነው ብለህ ያልታሰበውንና ያልተባለውን ተናግረሃል...* ለተባለው፤ እውነታው፤ ቤ/ክኑ ቻሪት ነው በቦርድ ኦፍ ትረስቲስ (ባላደራ) ነው መመራት ያለበት የሚሉ መረጃዎችና መንደርደሪያ የጥናት ክንውንኖች ውስጥ ለውስጥ እያካሄዳችሁ፤ እኛም መረጃውን ይዝን በግልጽ ስናፋጣችሁ፤ ምንም እንኳን የምግባረ ሰናይ ስራን ብትሰራም፣ ቤ/ክችን ታላቅ የእምነት ተቋም እንጂ ቻሪቲ ወይም ቦርድ አይደለችም! ባላደራዋም ክርስቶስ ስለሆን ሌላ ተቀጽላ ባላደራ አያስፈልጋትም! ከአባታችን ከአቡነ ዮሐንስ ጀምሮ ቀደም ስላለው የቤ/ክችን አስተዳደርና አሰራር ልምዱ ያልንን ካህናትና ምእመናንን በቅድሚያ ማወያየት ይገባል፤ ቻሪቲ ትሁን የምትሉ ከሆነ፣ ከታቦተ ህጉ ጀምሮ፣ ንዋያተ ቅዱሳቱ በሙሉ እስከ ጽናጽሉ ያቻሪት ንብረት እንደሚሆን ተረዱ! እያልን ድምጻችንን ስለ ቤ/ክን ስናሰማ፤ የእገሌ አሉባልታ ነው፣ ያልታሰበና ያልተባለ ነው፤ እያላችሁ ሽምጥጣችሁ እስከ መካድ መድረሳችሁ ያስገርማል።

የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔ በመሻር፣ የምግባረ ሰናይ ኮሚቴውን እንዳይቋቋም በሕገወጥነት ከማገድ ጀምሮ፤ ቤ/ክኑን ባልተሟላ ሰ/አ/ጉባዔና ያለ ሕጋዊ ጸሐፊ ለዓመታት ማቀየታችሁ፣ የሰ/ጉባዔው ቤ/ክኑን ወደፊት በባላደራ ቦርድ እንዲመራ አጀንዳ ተቀርጾ እያወያያችሁ ወዘተ... የምትፈጽሙት ተግባር ሕገወጥ መሆኑን፣ የሕግና ስነስርአት ጉባዔ በተደጋጋሚ የጻፈላችሁን ደብዳቤዎችና ያስተላለፉቸውን ውሳኔዎችን መመልከት ለመረዳት በቂ መረጃ ነው። ለማንኛውን ከማህደራችሁ ተደብቀው ካሉ መረጃዎቹ መካከል ጥቂት ኮፒ፣ ችግሩን በጥልቅ ላልተረዱ አሳሳቢነቱን ለመጠቆም ያህል በሚቀጥለው ገጽ ተያይዟል።

በሰበካ ጉባኤው ስላለ የቤ/ክናችን ገንዘብ መጥፋትና አያያዝ ችግር፣ ስለ ንብረት መባከንና አጠባበቅ፣ የቤ/ክ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ስለ መጣሱ፣ ቤ/ክናችን በሰበካ መ/አ/ጉባዔ እንጂ፣

ተጠሪነቱ ለቻሪቲ ኮሚሽን በሆነ የባላደራ ቦርድ መመራት የለባትም... ወዘተ በሚል በካህናትና ምእመናን ሃሳብና ጥያቄ ሲነሳ፤ በማድፈንፈንና አጀንዳውን ለመቀየር፣ እንደወቅቱ የሃገራችን መሪዎች፤ ጥያቄ በሚያነሳው ላይ የሃሰት ክስና የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄዱ ከእምነታችንም ሆነ ከሕግ አንጻር ተገቢ አይደለም። መፍትሄው ግን፡ የሃሰት ውንጀላውንና መጻጻፉን ትቶ፤ ሁሉንም የቤ/ክናችንን አባላት በጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት የቤ/ክንን ሕግና አንድነት የጠበቀ የስምምነት ውይይት በማድረግ የቤ/ክችንን መሠረት የጠበቀ የጋራ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ጥረት ማድረግ ብቻ ነው።

በዚህ መልኩ፡ ሁሉም ካህናትና ምእመናንን በማሳተፍ፤ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ማስፋፋት፡ በሕንጻ እድሳትና ልማት እየታየውን ያሉ በጎ ስራ ማጠናከር፣ በሰንበት ት/ቤቱ በኩል ያለውን ጥሩ እንቅስቃሴ በማጎልበት፣ ሁሉን በፍቅር በማቅረብ የቤ/ክችንን ግዢ እዳ ተረባርቦ መክፈልና፣ ለቤ/ክናችን እድገት በሕግና ባንድነት መስራት እንጂ፤ የሃሰት ክስና ስም ማጥፋት በቃልና በጽሁፍ በመደርደር ካህናትና ምእመናንን መከፋፈል ማጋጨት፣ ከታለመው አላማ የማያደርስ ከንቱ ድካምና፣ ትርፉ ቤ/ክችንን ለጭቅጭ፣ መለያየትና የከፋ ችግር ወደፊት መዳረግ ነው። ለክርስትና እምነታችንም ፍጹም ተቃራኒ ከመሆኑም በላይ፣ ከተጠራንበት መንፈሳዊ አላማ ውጭ መሆኑን በጥብቅ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

በቤ/ክን፤ የማይታይ የተሰወረ፣ የማይገለጥ የተከደነ፣ ይኖራል ብሎ ማሰብ በእምነት አለመብሰል ነውና!!

እግዚአብሔር ቤ/ክችንን ከጸላየ ሠናያት ይጠብቅልን!!

ዲ. ድርሻዬ ለማ።

<u>ግልባጭ፤</u>

- [illegible]
- ለካህናት ጉባዔ
- ለሕግና ሥነ ሥርዓት ጉባዔ
- ለቁጥጥር ኮሚቴ
- ለሕንጻና ልማት ኮሚቴ
- ለሰንበት ት/ቤት